

በ: ሀ. ሂለል
ምሳሌዎች: አቢኤል ባሲል
הוֹצָאָה: ספרית פועלים
የእድሜ ክልል: ታዳጊዎች

שִׂיחָה

ውይይት - የእኛ ሰንበት
መልካሙ የሰንበት ቀን ጥቂት ቆይቶ ወደ እኛ ይወርዳል"“
[ሰንበት፣ ሽሙኤል ባስ]
የሜዳ አህያዋ ታሪክ ሰንበት ስለሚያመጣው ልዩ ነገር ለመናገር እድል ይሰጣል። ታዳጊዎቹን በሰንበት ቀን ምን ማድረግ እንደሚወዱ መጠየቅና እናንተው ወላጆች የምትወዷቸውን ነገሮች አካፍላቸው።

מִשְׂחָק

በልብሶቹ የቁም ሳጥን ውስጥ
ሽሚዝ? የዋና ልብስ? ምናልባት ቀሚስ? – ወደ ቁም ሣጥኑ ውስጥ በመመልከት የሚወዷቸውን ልብሶች ይፈልጉና አብዛኛውን ጊዜ መቼ እንደሚለብሷቸው መተረክ ይኖርብዎታል፦ የክረምት ወይስ የበጋ ልብስ፣ የበዓል ዝግጅት ልብስና በተለዬ መልኩ የሚወዱት ልብስ።

שְׁמַע

ከሜዳ አህያዋ ጋር መዘመርና መደነስ

የ"የሜዳ አህያዋ ፒጃማ የምትለብሰው ለምንድን ነው?" ስንኞች የተዘጋጁ ሲሆን የልጆች ተወዳጅ ዘፈኖች ናቸው። አብራችሁ ለመዝፈንና ለመደነስ የQR ኮዱን ስካን ማድረግ አለባችሁ።

כְּלָלִי

ስዕላዊ መግለጫዎች - የሜዳ አህያና ጓደኞች

የሜዳ አህያዋ ጓደኞች በመጽሃፉ ውስጥ በተገለጹት ስዕላዊ መግለጫዎች ውስጥ ይታያሉ፡- አብረው ማሰስ፣ ጓደኞችን ማግኘት፣ የእንስሳትን ስም አንድ ላይ ማለትና እነርሱን መወከል ይችላሉ። በሚቀጥለው ደረጃ የሚታወቀውን እንስሳ ስም መጥቀስና በመጽሐፉ ውስጥ ባሉት ስዕላዊ መግለጫዎች ውስጥ መፈለግ ይችላሉ።